የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ፌ ዴ ራ ላ ዊ ዲ ሞ ክ ራ ሲ ያ ዊ ሪ ፐ ብ ሊ ክ

# የ ፌ ዴ ራ ል ጠ ቅ ላ ይ ፍ ር ድ ቤ ት

የሰበር መ/ቁ/ 224485

ግንቦት 19 ቀን 2014 ዓ.ም

የምርጫ ጉዳዮች ሰበር ሰሚ ችሎት

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፡-ወኪል ወንጌል አባተ ቀረቡ

ተጠሪ፡ አቶ አሰድ አህመድ ሁሴን፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍርድ</u>

መዝገቡ የቀረበዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል ዉሳኔዉ እንዲታረም አመልካች መጋቢት 29 ቀን 2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

ከስር ክርክሩ አመጣጥ ሲታይ በ6ኛዉ ሀገር አቀፍ ምርጫ በሶማሊ ክልል መስከረም 20 ቀን 2014ዓ.ም በተካሄደዉ ምርጫ በመዩ ሙሉቂ ምርጫ ክልል የተደረገው ምርጫ ጊዜያዊ ውጤት ከተገለጸ በኋላ የብልጽግና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ የሆኑት ወ/ሮ አያን አብዲ ባቀረቡት ቅሬታ በድምጽ መስጫ ዕለት መራጮች የፈለጉትን ፓርቲ ወይም ግለሰብ በነፃነት እንዳይመርጡ መከልከላቸውን፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች ጫና እንደነበረ፣ የድምፅ አሰጣጥ ስርዓት ህግን ያልተከተለ፣መስፈርት የማያሟሉ መራጮች እንዲመርጡ መደረጉ፣በመራጮች ላይ ዛቻና መስፈራሪያ እንደነበር፣የካቢኔና የሚሊሻ አባላት ዛቻና

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ

ማስፈራራት በመጠቀም መራጮች ለቅሬታ አቅራቢዋ የሰጧቸውን ድምጽ ከድምጽ ምርጫ ሳጥን ውስጥ እንዲወጣ በማድረግ የማጭበርበር ተግባር የተፈፀመባቸው መሆኑን በመግለጽ በዚህ ምርጫ ክልል የተካሄደው ምርጫ ውጤት ተሰርዞ ድጋሚ ምርጫ እንዲከናወን በሚል አቤቱታ ማቅረባቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ቦርዱም ማስረጃ መርምሮ በአቤቱታ አቅራቢዋ የጠቀሱት የህግና አሰራር ግድፈቶች መፈፀማቸውን አስረድተዋል በሚል በምርጫ ክልሉ በሌሎች የምርጫ ጣቢያዎች ከተወዳደሩት ዕጩዎች እና በቅሬታ አቅራቢዋ መካከል ያለው የውጤት ልዩነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን፤ተጭበርብረዋል የተባሉት ምርጫ ጣቢያዎች ድምጽ ሙሉ በሙሉ ለቅሬታ አቅራቢዋ ቢጨመርላቸው እንኳን አሸናፊ ሊሆኑ አይችሉም፤የምርጫ ክልሉንም ውጤት ሊቀይር አይችልም፤በሌሎች ምርጫ ጣቢያዎች ጥሰት ስለመኖሩ ደግሞ አቤቱታ አልቀረበም፤ስለዚህ የምርጫ ክልሉን የምርጫ ውጤት ሊያሰርዝና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ የሚያስደርግ አይደለም ካለ በኋላ ይሁን እንጂ ከኦዲት ቡድን ምርመራ የቀረበው የኦዲት ምርመራ ውጤት በመመርመርና የምርጫውን አጠቃላይ ሂደትና ውጤት ትክክለኛነትና ታማኝነት የበለጠ ለማረጋገጥ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ምርመራ መደረግ እንዳለበት እናም በሙዩ ሙሉቄ ምርጫ ክልል የተደረገው የምርጫ ውጤት አጠቃላይ ድጋሚ ቆጠራ እንዲደረግ በማለት ቦርዱ በቀን 02/02/2014 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ መሰረት የተደረገዉን የድምጽ ቆጠራ እና ኦዲት ምርመራ ሪፖርት የምርጫ ቦርዱ ድጋሚ ገምግሞ በሙዩ ሙሉቄ ምርጫ ክልል መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም የተካሄደው ምርጫ ጥሰት የተፈፀመበት ነዉ በማለት በምርጫ ክልሉ ድጋሜ ምርጫ እንዲካሄድ ህዳር 3 ቀን 2014ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በምርጫ ክልሉ ለክልል ምክር ቤት ምርጫ የግል ተወዳዳሪ ሲሆኑ ቦርዱ ውሳኔ የሰጠዉ በገልለተኛ ማስረጃ ሳያጣራ ነዉ በሚል ጉዳዩ እንደገና እንዲመረመር ያቀረቡትን አቤቱታ ቦርዶ መርምሮ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚታይ ነዉ በማለት ህዳር 27 ቀን 2014ዓ.ም የተጻፈ ምላሽ መስጠቱን ተከትሎ ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር ሰምቶ ከስር መዝገብ ጋር መርምሮ አቤቱታ አቅራቢዋ ወ/ሮ አያን አብዲ ሹኩር የብልጽግና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ሆነው በምርጫ ክልሉ ለክልል ምክር ቤት የተወዳደሩ መሆኑን፤ተወዳዳሪዋ አቤቱታ ያቀረቡት ፓርቲያቸውን ወክለው አለመሆኑን በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(1) መሰረት የድምጽ ቆጠራ እና ዉጤት ላይ አቤቱታ ለማቅረብ መብት



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
The Federal Supreme Court Federal Democratic Republic of Ethiopia
ሰበር 2
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 23/02/14

የተሠጣቸው ለፖለቲካ ድርጅቶች፣ ለግል ዕጩ ወይም ለሕጋዊ ወኪል በመሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የፓርቲው ወኪል ሳይሆኑ በግላቸው በምርጫ ውጤቱ ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብት **(standing right)** የላቸውም፡፡ስለዚህ ግለሰቧ አቤቱታ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ቦርዱም አቤቱታቸውን ውድቅ ማድረግ ሲገባው አቤቱታቸውን ተቀብሎ የክልሉ ምርጫ ውጤት በመሰረዝ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ውሳኔ መስጠቱ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት የቦርዱ ውሳኔ ሽሯል፡፡

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡ውሳኔዉ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት ያልተነሳውን ስነ-ስርዓታዊ ጉዳይ በራሱ በማንሳት ቅሬታ አቅራቢዋ በግሏ አቤቱታ ማቅረብ አትችልም ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ተጠሪ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ 10 ቀን ካለፈ በኋላ በመሆኑ አመልካች መጀመሪያ መልስ ሲሰጥ የይርጋ መቃወሚያ ያላቀረበ መሆኑን በማመልከት በስነ-ስርዓታዊ ይርጋ ክሱን ውድቅ ለማድረግ እንዲቻል አቤቱታ ለማሻሻል ያቀረበውን ጥያቄ አላግባብ ውድቅ ማድረጉን እንዲሁም ስነ-ስርዓታዊ ይርጋን ፍርድ ቤቱ በራሱ በማንሳት ይግባኙን ውድቅ አለማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(1) መሰረት በድምፅ ቆጠራ ሂደት እና ውጤት ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ወይም ወኪል ቅሬታ ማቅረብ እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡በተጨማሪም በአጠቃላይ የምርጫ ሂደት ላይ ቅሬታ የቀረበ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 154(5) ላይ የአንድን መራጭ ድምጽ መስጠት የሚቃወም ሰው አቤቱታውን በየደረጃው የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት መብት እንዳለው የተደነገገ መሆኑን፤ይህ ደግሞ በምርጫ ተሳታፊ የነበረ ዕጩን እንደሚያካትት የሚያከራክር ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ቅሬታ የቀረበው በምርጫ ውጤት ብቻ ላይ እንደሆነ በመቁጠር የፓርቲ ዕጩ ቅሬታ ማቅረብ አይችሉም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች የይርጋ ጥያቄ በማንሳት መልስ ለማሻሻል ጥያቄ አቅርቦ የታለፈበትን እና የብልፅግና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ቅሬታ ያቀረቡት በምርጫ ውጤት ላይ ብቻ ሳይሆን በሂደቱም ጭምር በሆነበት ስር ፍ/ቤት አቤቱታ አቅራቢዋ በግላቸው አቤቱታ ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 91(2) ከአዋጅ ቁ.1162/2011 አንቀጽ 154(5) አንፃር መጣራት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር 2
The Federal Supreme Court
Federal Democratic Republic of Ethiopia

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 23/09/14

ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 19/08/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ተጠሪ በምርጫ ቦርድ በነበረው ክርክር ያልተጠራ ወይም በመልስ ሰጪነት በክርክር ሂደቱ ያልተሳተፈ የአንድ ወገን ክርክር ብቻ ሰምቶ ውሳኔ መስጠቱ፣ አቤቱታ አቅራቢዋ በእጩነት ያቀረበው ብልፅግና ፓርቲ ውክልና እና ፍቃድ ያልሰጣቸው ስለመሆኑ፣ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 91 መሰረት አቤቱታ ወይም መልስ ማሻሻል የሚቻለው አስቀድሞ የቀረበ ክርክር ለማብራራት ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚያግዝ ሲሆን እንጂ አመልካች መልሳቸውን ለማሻሻል ያቀረቡት ምክንያት በመጀመሪያ መልስ ያልተጠቀሰ የይርጋ መቃወሚያ አዲስ ክርክር ለማቅረብ ሲሆን ይህም ለማብራሪያ ወይም ለትክክለኛ ፍትህ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን መልስ ለማሻሻል አቤቱታ አለመቀበሉ አግባብና ስነ-ስርዓታዊ በመሆኑ የሚነቀፍ አለመሆኑን፤የምርጫ ውጤቱ እንዲሰረዝ ውሳኔ የተሰጠው የምርጫ ክልሉ ላይ አሸናፊ የሆነው ተጠሪ በሌለበት ሲሆን ተጠሪ የምርጫ ውጤቱ መሰረዙ ያወቀው በህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም መሆኑንና ውሳኔውን ከሰሙ በ10 ቀን ውስጥ ተጠሪ ይግባኝ ያቀረበ በመሆኑ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ሳይሆን ውሳኔው መኖሩን ተጠሪ ካወቀበት እና በሌለበት የተሰጠ ውሳኔ ተነስቶ ክርክር እንዲገባ ጥያቄ አቅርቦ ውድቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በመሆኑ የይርጋ ጊዜ አላለፈም፡፡በአዋጁ አንቀጽ 151፣ 152 እና 154 ድንጋጌዎች በቅድመ ምርጫ እና በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ላይ እያለ ቅሬታ ያለው አካል ምርጫውን ለማስቆም ቅሬታ የሚቀርብበት ስርዓት የሚመለከት ሲሆን አንቀጽ 155 ደግም በድህረ ምርጫ ሂደት ማለትም በድምጽ ቆጠራ እና ውጤት ላይ ቅሬታ ለማቅረብ ስርዓትን ዘርግቷል፡፡የብልፅገና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ቅሬታ ያቀረቡት ምርጫው ተጠናቆ ድምጽ ቆጠራ ከተከናወነ እና አሸናፊ ከተለየ በኋላ በመሆኑ ቅሬታቸው ሊስተናገድ የሚገባው በአንቀጽ 155 እንጂ በአንቀጽ 154 አይደለም፤ በአንቀጽ 155 ደግሞ ቅሬታ የማቅረብ መብት የተሰጠው የፖለቲካ ድርጅት፣ የግል ዕጩ ወይም ወኪል ብቻ ሲሆን የብልጽግና ፓርቲ እጩ በራሳቸው ቅሬታ የማቅረብ አልተሰጣቸውም፤ስለዚህ የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Supreme Court
4
ሰበር 2

ፌዴራል ... ቤት
ትክክል ግ...
ፊርማ ... ቀን 23/09/14

ሠ591

የጉዳዩ አመጣጥ እና ግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በመዩ ሙሉቄ ምርጫ ክልል የተደረገው ምርጫ ድምጽ ቆጠራ ተደርጎ ጊዜያዊ ውጤት ከተገለጸ በኋላ የብልጽግና ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ የሆኑት ወ/ሮ አያን አብዲ በግል አቤቱታ ለማቅረብ መብት የላቸዉም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ የምርጫ ህጉንና የስነስርዓት ህጉን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለሰበር ችሎት ከተሰጠዉ ስልጣን አኳያ ተመልክተናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት ዋና ዓላማ በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እና አተገባበር እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም መስጠቱ (አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል) ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ አገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የሚያስችል ነዉ፡፡መሰረታዊ ህግ ስህተት ምንድነዉ? ለሚለዉ በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር ከሀ-ሸ የተመለከተ ሲሆን በሰበር ችሎቱ ሊታዩ የሚችል የመጨረሻ ዉሳኔ፣ፍርድ፣ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ ህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ህግን አለ አግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋና ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፣ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር 2 The Federal Supreme Court Federal Democratic Republic of Ethiopia

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ... 23/09/14

በመቃረን የተወሰነ ዉሳኔ ጉዳይ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ስለዚህም ለሰበር የቀረበዉ ጉዳይ ከእነዚህ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ እንደሚያሣየን የቅሬታዉ መነሻ የድምጽ ቆጠራ ሂደትና ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡በምርጫ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች እና አቤቱታዎች የሚስተናገዱበት ስርዓት የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡(አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 151-155 ያሉትን ድንጋጌዎች ይመለከቷል)፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በምርጫ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች እና የሚቀርቡ አቤቱታዎች በሶስት ደረጃዎች ተከፍለዉ የሚታዩ ሲሆን እነዚህም በቅደም ተከተል ቅድመ ምርጫ ማለትም መራጮች እና እጩዎች ምዝገባ ሂደት፣የምርጫ ሂደት እና ድህረ ምርጫ ማለትም ድምጽ ቆጠራ እና ዉጤት ሂደት ናቸዉ፡፡በእነዚህ ሂደቶች ዉስጥ የሚነሱ ክርክሮች ወይም ቅሬታዎች በየደረጃዉ የሚመለከቱ አካላት ተለይተዉ የተገለጹ ሲሆን አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜም ሆነ አቤቱታ ለማቅረብ የሚችለዉ አካል ማን እንደሆነም ጭምር ተመላክቷል፡፡ስለዚህም በምርጫ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች እና ቅሬታዎችን ተመልክተዉ ዉሳኔ እንዲሰጡ ስልጣን የተሰጣቸዉ አካላት የቀረበላቸዉን አቤቱታ ወይም ክርክር በመመርመር ሂደት ዉስጥ መሰረታዊ የሆኑ የስነስርዓት ጉዳዮች ማለትም አቤቱታ ያቀረበዉ ወገን በህግ መብት የተሰጠዉ ሰዉ መሆን አለመሆኑን፣ አቤቱታዉ በህጉ የተገለጸዉን ጊዜ ጠብቆ የቀረበ መሆኑን እንዲሁም መሰረታዊ የሆነዉን የመሰማት መብት ጭምር ማክበር እና የማስከበር ሃላፊነት እንዳለባቸዉ እሙን ነዉ፡፡ከላይ እንደተገለጸዉ ለቦርዱ ቅሬታ የቀረበዉ የድምጽ ቆጠራ ተደርጎ ዉጤት ከተገለጸ በኋላ ነዉ፡፡በድምጽ ቆጠራ ሂደትና ዉጤት ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት የፖለቲካ ድርጅት፣የግል እጩ ወይም ወኪል ብቻ ስለመሆኑ አዋጁ በግልጽ ደንግጓል፡፡(አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(1) ይመለከታል)፡፡ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ከአንቀጽ 154(5) ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በሚል ጭብጥ ይዟል፡፡ከላይ እንደተመለከትነዉ የምርጫ ሂደት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች እና ክርክሮች ከጉዳዩ ልዩ ባሕርይና በተለይም ጊዜ አንዱ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ በደረጃ ተለይቶ የቅሬታ አቀራረቡም ሆነ ጊዜ ተወስኖለት ተቀምጧል፡፡የአዋጁ አንቀጽ 154 ተፈጻሚነት በድምጽ አሰጣጥ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች ላይ ነዉ፡፡አሁን የቀረበዉ ጉዳይ የድምጽ ቆጠራና ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ ረገድ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የአዋጅ አንቀጽ 155 ድንጋጌ ግልጽ በመሆኑ ትርጉም የሚያስፈልገዉ ሆኖ አላገኘንም፡፡የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ህጉ ግልጽ በሆነ ጊዜ ይህንኑ ገቢራዊ ማድረግ እንጂ ትርጉም መስጠት

ሰበር 2
Federal Supreme Court
The Federal Democratic Republic

ፌደራል ጠቅላ... ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ... ቀን 23/09/14

እንደማይጠበቅበት የህግ አተረጓጎም መርህ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነዉ፡፡ስለዚህም የብልጽግና ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ የሆኑት ግለሰብ በድምጽ ቆጠራና ዉጤት ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ ከመመርመሩ በፊት ግለሰቧ የድምጽ ቆጣሪ ሂደትና ዉጤት ላይ ቅሬታ የማቅረብ መብት ያላቸዉ መሆን አለመሆኑን ከዚህ ድንጋጌ አኳያ በመመርመር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሌላዉ የአመልካች ቅሬታ ነጥብ እና ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉ ጭብጥ አመልካቹ መልሱን ለማሻሻል ያቀረበዉ አቤቱታ የታለፈበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ከመዝገቡ እንደተገነዘብነዉ አመልካች በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመልስ ሰጪነት ተጠርቶ መልሱን በጽሁፍ ካቀረበ በኋላ ማብራሪያ ለመስጠት በሚል መልሱን ለማሻሻል እንዲፈቀድለት ያቀረበዉን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ መርምሮ ማብራሪያዉን ክርክር በሚሰማበት ጊዜ ለማቅረብ እድል እንዳለዉ በማመላከት ያለፈዉ ስለመሆኑ ችሎቱ በቀን 08/06/2014ዓ.ም በመዝገቡ ላይ የሰጠዉ ትእዛዝ ይዘት ያመለክታል፡፡በዚህ አግባብ ክርክሩ በቃል በተሰማበት ጊዜም አመልካች የበኩሉን ክርክር ማሰማቱን መዝገቡ ያሣያል፡፡ አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረዉ በአንድ በኩል ተጠሪ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበዉ 10 ቀን ካለፈ በኋላ በመሆኑ እና የስነ ስርዓት ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በራሱ ማንሳት ይገባ እንደነበር በሌላ በኩል መልሱን በማሻሻል የስነ ስርዓት ይርጋ በመቃወሚያነት ሊያነሳ ይችል እንደነበር በመጥቀስ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ ከክርክሩ እንደተገነዘብነዉ ቦርዱ ህዳር 3 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ ተጠሪ ሳይሳተፍበትና ሳይጣራ ነዉ በሚል ተጠሪ ለቦርዱ አቤቱታ አቅርቦ ቦርዱም የተጠሪን ቅሬታ ባለመቀበል በ27/03/2014ዓ.ም ምላሽ በመስጠቱ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ይግባኙን በ04/04/2014ዓ.ም ማቅረቡን መዝገቡ ያሣያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የቦርዱ ዉሳኔ በጽሁፍ ለተጠሪ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ ሲታሰብ ጊዜዉ ያላለፈበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሰረቱ፡ ምርጫ ጉዳይ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ወይም ክርክሮችን የመመርመር እና የመወሰን ስልጣን የተሰጣቸዉ አካላት ዉሳኔዉያቸዉን በጽሁፍ እንዲያሳየዉቁ በህጉ የተመለከተዉ ይህንኑ መብት ለማስከበር እንዲቻል ተብሎ ነዉ፡፡የይግባኝ ጊዜ አቆጣጠር በሚመለከት በዉሳኔ ሰጪ አካል ምክንያት የሚባክን ጊዜ ተከራካሪ ወገን ጉድለት ተደርጎ መታሰብ እንደማይገባ እንዲሁም የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን ላይ ጊዜዉ መታሰብ የሚገባዉ ዉሳኔዉን ካወቀበት ቀን ሊሆን እንደሚገባ በማመላከት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነዉ፡፡(በሰበር መዝገብ ቁጥር 87190፡83915 ቅጽ 15 እና ሌሎች መዝገቦችን መመልከት ይቻላል)፡፡በዚህም ጉዳይ

ሰበር 2
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 23/08
ፊርማ

አመልካች ለይግባኝ ሰሚ ችሎት ባቀረበዉ መልስ ላይ ይግባኙ የቀረበዉ ከ10 ቀን በኋላ ነዉ የሚለዉ ቦርዶ ዉጤት እንዲሰረዝ ከወሰነበት ህዳር 3 ቀን 2014ዓ.ም ጀምሮ በመቁጠር እንጂ ተጠሪ ለቦርዱ ባቀረበዉ አቤቱታ ላይ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚታይ ነዉ በማለት ቦርዱ በ27/03/2014ዓ.ም የሰጠዉን ምላሽ ከግምት ያስገባ ባለመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ወደ ስረነገር ክርክሩ ሳይገባ በስነስርዓት ጉዳይ ላይ ተመርኩዞ የሰጠዉ ዉሳኔ በክርክር አመራር ረገድ ፍርድ ቤቶች ክርክሩን በስነስርዓት ህግ መሰረት ለመምራትና ለመቆጣጠር የተሰጣቸዉን ስልጣንና ሃላፊነት ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10(1) ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ በዉሳኔዉ ላይ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/217483 ላይ በቀን 22/06/2014ዓ.ም የሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ፌደራል ጠቅላ... ቤት ትክክለኛ ግ... 23/08/14 ፊርማ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Supreme Court ሰበር 2